**Colorado የመለያ ሥራ ማስቆሚያ ፖሊሲ**

Instacart ከሙሉ አገልግሎት ሸማቾች ("ሸማቾች") ጋር ባለው ግንኙነት የሚኮራ ሲሆን የደንበኞችን ፍላጎቶች ከሚያሟሉ እና ከዚያም የበለጠ ብቃት ካላቸው፣ የዘርፉን ልምዶች ከሚከተሉ፣ እና ተፈጻሚ የሆኑ ሕጋዊ ቅድመ ሁኔታዎችን ከሚያሟሉ ሸማቾች ጋር አጋርነት መፍጠር ይፈልጋል።

ከሸማቾች ጋር ላለን ግንኙነት ዋጋ ስለምንሰጥ በInstacart አገልግሎቶችን ከሚያቀርቡ ሸማቾች ስለሚጠበቁ ነገሮች ግልጽ መሆን እንፈልጋለን፤ ይህም በተለየ የሸማች መለያ እንዲታገድ ወይም ሥራ እንዲያቆም የሚያስደርጉ እንቅስቃሴዎችን እና የእንቅስቃሴ ዓይነቶችን ወይም ካልሆነ የሸማችን የአገልግሎት ዕድሎች የመጠቀም መብት የሚገድቡ ተግባራት ላይ ነው።

## ደረጃዎች

ሸማቾች በሚያቀርቧቸው አገልግሎቶች መሠረት ደረጃ ሊሰጣቸው ይችላል። Instacart የደረጃ አሰጣጥ ሥርዓት ሲያስጀምር ሥርዓቱ ምን እንደሚያስቀምጥ፣ የደረጃ አሰጣጡ እንዴት እንደሚሰላ፣ እንዲሁም ደረጃ አሰጣጡ እንዴት ሸማቾች ላይ ተጽእኖ እንደሚያሳድር ለሸማቾች እናሳውቃለን። ሸማቾች አነስተኛ ደረጃ ስላገኙ ብቻ መለያቸው አይታገድም ወይም ሥራ እንዲያቆም አይደረግም፤ ነገር ግን ከፍተኛ ደረጃ ካገኙ የአገልግሎቶችን እድሎች ለማግኘት ቅድሚያ ሊሰጣቸው ወይም አነስተኛ ደረጃ በማግኘታቸው የበለጠ የተገደበ የአገልግሎት እድሎች ሊገጥማቸው ይችላል።

## የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎች

ሁሉም ሸማቾች በ Instacart ሦስተኛ ወገን የኋላ ታሪክ አጣሪ አካላት ለሚደረግ የኋላ ታሪክ የማጣራት ሥራ ፈቃዳቸውን ይሰጣሉ። ሸማቾች በInstacart በኩል የአገልግሎቶች እድል ለማግኘት በቅድሚያ የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎችን ማለፍ አለባቸው። በተጨማሪም ሸማቾች ተከታይ ለሆነ የኋላ ታሪክ ማጣሪያ ፈቃዳቸውን ይሰጣሉ፣ ከዚያም እነዚያን የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎች ሲያልፉ ቀጣይነት ያለው የInstacart መድረክን የመጠቀም እድል ያገኛሉ። በሌላ አገላለጽ ሸማቾች የኋላ ታሪክ ማጣሪያዎችን ከወደቁ መለያቸው ሊታገድ ወይም ሥራ እንዲያቆም ሊደረግ ይችላል። ተፈጻሚ ለሆኑ ሕጋዊ ቅድመ ሁኔታዎች ተገዢ በመሆን ሸማቾች የኋላ ታሪክ ማጣሪያን ሊወድቁባቸው የሚችሉባቸው የተለመዱ ምክንያቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፣ ነገር ግን በእነዚህ ምክንያቶች ብቻ የተገደበ አይደለም፦

- የቅርብ ጊዜ የከባድ ወንጀሎች ፍርድ፤
- የቅርብ ጊዜ ከባድ የወንጀል ድርጊቶች፤
- የቅርብ ጊዜ የከባድ ወንጀል ክሶች፣ በሂደት ላይ ያሉ፤
- በርካታ የቅርብ ጊዜ የመኪና ማሽከርከር የሕግ ጥሰቶች፤
- የቅርብ ጊዜ ከባድ የመኪና ማሽከርከር የሕግ ጥሰቶች፤ እና
- የታገደ ወይም የማያገለግል የመንጃ ፈቃድ።

## የማንነት ማጣሪያዎች

Instacart አገልግሎቱን የሚያቀርበው ሸማች ከሸማች መለያው ጋር የተያያዘው ግለሰብ መሆኑን ለማረጋገጥ የሰልፊ (የፊት ካሜራ ፎቶግራፍ) ማጣሪያዎች በመባልም የሚታወቁትን የማንነት ማጣሪያዎች ያካሂዳል። በማንነት ማጣሪያ የተነሳው ፎቶግራፍ የሸማቹ የመለያ ፎቶግራፍ ላይ ያለው ግለሰብ መሆን አለበት። ሸማቾች የማንነት ማጣሪያን ከወደቁ መለያቸው ሊታገድ ወይም ሥራ እንዲያቆም ሊደረግ ይችላል። የማንነት ማጣሪያን የሚወድቁባቸው የተለመዱ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- በማንነት ማጣሪያ የተነሳው የፊት ገጽታ ከሸማቹ የመለያ ፎቶግራፍ ጋር ተመሳሳይ ካልሆነ፤
- በማንነት ማጣሪያው የተነሳው የፊት ገጽታ በወቅቱ የተነሳ የፊት ገጽታ ሳይሆን ከፎቶግራፍ ላይ የተነሳ ከሆነ፤ እና
- በማንነት ማጣሪያው የተነሳው የፊት ገጽታ ብዥ ያለ ወይም የማይታይ ከሆነ።

**ደኅንነት**

የInstacart መድረክን የሚጠቀሙ (ለምሳሌ፦ ሸማቾች፣ ደንበኞች፣ ቸርቻሪዎች) እና በአጠቃላይ የሕዝቡ ደኅንነት መጠበቅ Instacart ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። የInstacart መድረክን ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ እንዲረዳው Instacart ሌሎችን ሊጎዳ የሚችል ወይም አደገኛ ሁኔታዎችን የሚፈጥር እንቅስቃሴን ይከለክላል። ከደኅንነት ጋር በተያያዙ በሚከተሉት ማናቸውም ተግባራት ምክንያት የሸማች መለያ ሊታገድ ወይም ሥራ እንዲያቆም ሊደረግ፣ ወይም የሸማቹ የአገልግሎት እድሎች የማግኘት እድሉ የተገደበ ሊሆን ይችላል፦

- የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ነገር ግን በሚከተሉት ብቻ የማይገደብ ብጥብጥ / ጥቃት፦
    - ይህንን ገደብ የሚከለክል የግዛት ሕግ ከሌለ በስተቀር በInstacart በኩል አገልግሎት ሲሰጡ የጦር መሣሪያ መያዝ ወይም በሌላ መንገድ በችርቻሮ ሻጭ ወይም ደንበኛ ግቢ ውስጥ የጦር መሣሪያ መያዝ፤
    - ጥቃት፣ ብጥብጥ ወይም ጥቃት የማድረስ ማስፈራሪያ፤
    - ጸብ አጫሪ ሁኔታዎችን ማሳየት፤
    - ሌላን ሰው የማጥቃት ወይም የማስፈራራት አያያዞች፤
    - ስለ ገንዘብ፣ ክፍያ ወይም የገንዘብ ጉርሻ ጨምሮ ደንበኞችን ማስጨነቅ፤
- ስርቆት / የሱቅ ስርቆት፤
- ጸያፍ ንግግር፤
- የደንበኞችን፣ የሌሎች ሸማቾችን፣ የችርቻሮ ሻጭ ተቀጣሪዎችን ወይም የInstacart ሠራተኞችን ከመጠን በላይ ግላዊ ጥያቄዎችን መጠየቅን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚያ ብቻ ያልተገደበ፣ ያልተፈለገ የቃል ወይም የጽሑፍ ግንኙነት፤
- በደንበኞች ፣ በሌሎች ሸማቾች፣ በችርቻሮ ሻጭ ተቀጣሪዎች፣ ወይም በInstacart ሠራተኞች ላይ አላስፈላጊ አካላዊ ንክኪ ማድረግ፣ ወሲባዊ ባሕርይ ማሳየት ወይም ማንኛውንም ዓይነት ትንኮሳ ማድረግ፤
- አገልግሎቶችን በሚሰጡበት ጊዜ አልኮልን ወይም አደንዛዥ እጾችን መጠቀም፣ ወይም በአልኮል ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ቁጥጥር ሥር ሆነው አገልግሎት መስጠት፤
- የንብረት ውድመት፤
- አስከፊ እንቅስቃሴዎች፣ ስድብ፣ ወይም ሌላ በማንኛውም በሚመለከተው ሕግ የሚጠበቅ ምድብ (ዘር፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ወ.ዘ.ተ.) ላይ ተመሥርተው ያልተፈለገ ድርጊትን መፈጸምን ጨምሮ ትንኮሳ ወይም አድሎአዊ ድርጊት፤
- አገልግሎቶችን በሚሰጡበት ጊዜ የInstacart ሸማች መለያ የሌላቸውን ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጨምሮ ማንኛውንም ሰው ይዘው መምጣት፤ እና
- የምግብ ማሸጊያዎችን መቀየር፣ በችርቻሮ የማይሸጡ ነገሮችን በከረጢቶች ውስጥ ማስቀመጥ እና የታሸጉ ከረጢቶችን መያዛቸውን ማረጋገጥ አለመቻልን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይገደብ፣ የምግብ ደህንነትን አደጋ ላይ መጣል።

## ተፈጻሚ የሆነ ሕግን ወይም ደንብን መጣስ

አንድ ሸማች በInstacart መድረክ በኩል አገልግሎቶችን በሚሰጥበት ጊዜ የፌደራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ሕግን ወይም ደንብን ከጣሰ መለያው ሊታገድ ወይም ሥራ እንዲያቆም ሊደረግ ወይም የአገልግሎት እድሎች ገደቦች ሊደረጉበት ይችላል። ምሳሌዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፣ ነገር ግን በምሳሌዎቹ ብቻ ሁኔታው አይገደብም፦

- በInstacart መድረክ በኩል አገልግሎቶችን በሚሰጥበት ጊዜ ማንኛውንም የፌዴራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ሕግ ወይም ደንቦችን መጣስ፤
- ከInstacart ጋር በሚደረገው የሸማች ገለልተኛ አገልግሎት ሰጪ ስምምነት ላይ በተቀመጠው መሠረት በቂ የመድን ሽፋን አለመያዝ፤
- በክብደት ተለክተው የሚሸጡ እቃዎች በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና ደንቦችን እንዲሁም የሚመለከታቸውን ፖሊሲዎች አለማክበር (ለምሳሌ፦ የእቃውን ክብደት በትክክል አለማስገባት፣ ትክክለኛ የደረሰኝ ምስሎችን አለመጫን፣ ወ.ዘ.ተ.)፤
- በInstacart መድረክ አልኮል ለማድረስ ለሚመርጡ ሸማቾች (እንዲህ ዓይነት እቃዎችን ማድረስ በሕጋዊ መንገድ በሚፈቀድባቸው አካባቢዎች)፣ አግባብነት ያላቸውን የአልኮል ሕጎች እና መመሪያዎችን አለማክበር (ለምሳሌ፦ መታወቂያ አለመፈተሽ፣ የደንበኛ ፊርማን አስመስሎ መፈረም፣ አልኮሆል የያዘን ትእዛዝ ክትትል ሳይደረግበት ማድረስ፣ ለአካለ መጠን ላልደረሰ ወይም በሚታይ ሁኔታ ለሰከረ ወይም በእጾች ተጽእኖ ሥር ለሆነ ሰው አልኮል ማድረስ፣ ሳይፈቀድለት አልኮልን መተካት፣ ወ.ዘ.ተ.)፤ እና
- በInstacart መድረክ በኩል በሐኪም ማዘዣ የተዘረዘሩ እቃዎችን ለማድረስ ለሚመርጡ ሸማቾች፣ የ1996 የጤና መድን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ሕግን ጨምሮ እና በInstacart የማዕቀብ ፖሊሲ ላይ እንደተገለጸው አግባብነት ያላቸውን የግላዊነት እና የመረጃ ደኅንነት ሕጎች እና ደንቦችን አለማክበር። ይህ መታወቂያን ከማጣራት ወይም በሐኪም ማዘዣ ላይ የተዘረዘሩ እቃዎችን የማድረስ ትእዛዝ ያለ ክትትል መተው ጋር የተያያዙ ተፈጻሚ የሆኑ የሐኪም ማዘዣ እቃዎችን የማድረስ ሕጎችን እና ደንቦችን አለማክበርን ያጠቃልላል።

## የወሲባዊ ትንኮሳ ጥሰቶች

Instacart የሚከተሉትን ጨምሮ ወሲባዊ ትንኮሳን የሚፈጥር ማንኛውንም ዓይነት ባሕርይን አይፈቅድም እንዲሁም እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ ወደ መለያ እገዳ ወይም ሥራ ማቋረጥ ወይም የአገልግሎት እድሎች መገደብ ሊያመራ ይችላል፦

- ያልተፈለገ ወሲባዊ እንቅስቃሴን መጀመር፤
- ወሲባዊ ሀሳብ የሚያሳይ አስተያየት ወይም የሰውነት እንቅስቃሴ፣ ወሲባዊ ሀሳብን የሚያቀርቡ ነገሮችን፣ ሥዕሎችን፣ ካርቱን፣ ፖስተሮችን ወይም ሌሎች ምስሎችን ማሳየት፤
- የሚያንቋሽሹ አስተያየቶች፣ መግለጫዎች፣ ስድቦች ወይም ቀልዶች፤
- ሰቅጣጭ አስተያየቶች፣ ወሲባዊ በሆነ መንገድ አዋራጅ የሆኑ ቃላት፣ ወይም ወሲባዊ ሀሳብ የሚያቀርቡ ወይም ጸያፍ መልዕክቶች መጻፍ ወይም ግብዣዎች ማቅረብ፤ እና
- አካላዊ ንክኪ ማድረግ ወይም ጥቃት ማድረስ፣ እንዲሁም እንቅስቃሴዎችን መከልከል ወይም መገደብ።

## ተቀባይነት ያላቸውን የአገልግሎት ደረጃዎች ማሟላት አለመቻል

የInstacart መድረክን የሚጠቀሙ ደንበኞች ጥራት ያለው አገልግሎት ይጠብቃሉ። በዚህ ምክንያት፣ የሚከተሉትን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚያ ብቻ ሳይገደብ፣ የተቀመጡ ዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃዎችን ለማሟላት አለመቻል፣ የመለያ መታገድን፣ ሥራ እንዲያቋርጥ መደረግን ወይም የአገልግሎት እድሎችን መገደብን ሊያስከትል ይችላል፦

- ተደጋጋሚ የደንበኛ ወይም የቾርቻሮ ሻጭ ቅሬታ የሚያስከትሉ አገልግሎቶችን መስጠት፤
- በሙቀት ወይም በቀዝቃዛ የሙቀት መጠን መቀመጥ ያለባቸውን ምግቦች ለመከላከል የታሸጉ ከረጢቶችን አለመጠቀም፣ ወይም የጭስ ሽታ ያላቸውን ምርቶች ማድረስን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚያ ብቻ ስይገደብ፣ የምግብ ደኅንነትን በተመለከተ የኢንዱስትሪ ደንቦችን አለማክበር፤
- በተደጋጋሚ በደንበኛው ዝርዝር መሠረት ትዕዛዞችን አለማቅረብ፤ እና
- በተደጋጋሚ ትእዛዝ ከተቀበሉ በኋላ ትእዛዝን አለማጠናቀቅ።

## የምስጢራዊነት ጥሰቶች

ሸማቾች በInstacart መድረክ ላይ የደንበኞችን ግላዊ መረጃ መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል። የምስጢራዊነት ጥሰቶች በተለያዩ መንገዶች ሊከሰቱ ይችላሉ። ለምሳሌ፦ አንድ ሸማች የደንበኛን ወይም የሌላን ሸማች ማንነትን ወይም አድራሻን ለሌሎች በማጋራት፣ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ የInstacart ሸማች መለያ የሌለውን ማንኛውንም ሰው በማምጣት፣ ወይም በሸማች መተግበሪያ (ሾፐር አፕ) የደንበኛ መረጃን ወይም ሌላ በግል የሚለይ ወይም ሚስጥራዊነት ያለው መረጃ በሚያሳይበት ጊዜ የስክሪን ምስል (ስክሪን ሻት) ማንሳት እና/ ወይም የተነሳ የስክሪን ምስል በማጋራት የገለልተኛ አገልግሎት ሰጪ ስምምነትን ሊጥስ ይችላል።

በተጨማሪም፣ የሸማች መተግበሪያ ከደንበኛው ትዕዛዝ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ *ለምሳሌ፦* ስለ እቃዎቹ፣ ትእዛዙ ስላለበት ሁኔታ፣ ወይም እቃው እንዴት ወደ ደንበኛው መድረስ እንዳለበት የመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ከደንበኞች ጋር ለመነጋገር ወይም ለመግባባት ካልሆነ በስተቀር ጥቅም ላይ መዋል የለበትም። እንዲሁም በማንኛውም ምክንያት ከደንበኛ ያልተጠናቀቀ ትዕዛዝ ጋር ባልተገናኘ በማንኛውም ምክንያት ደንበኛን ከሸማች መተግበሪያ ውጭ ለማግኘት በሸማች መተግበሪያ በኩል የተገኙትን የደንበኛን ምስጢራዊ እና/ወይም ግላዊ መረጃዎችን መጠቀም በገለልተኛ አገልግሎት ሰጪ ስምምነት ሥር ያለውን የሸማችን ምስጢራዊነት ግዴታ መጣስ ነው።

በመጨረሻም፣ በሸማች መተግበሪያ ውስጥ ምስጢራዊ እና/ወይም ግላዊ መረጃን በተሻለ ሁኔታ ለመጠበቅ ሸማቾች በተንቀሳቃሽ ስልካቸው ላይ ደኅንነቱ የተጠበቀ የይለፍ ቃል ሊኖራቸው እና ያልተፈቀደላቸው ወገኖች ምስጢራዊ እና/ወይም ግላዊ መረጃን በሸማች መተግበሪያ በኩል እንዳያገኙ ለማድረግ ምንም ዓይነት መተግበሪያው ላይ የሚያገለግሉ ኮዶችን ለሌሎች አለማጋራት ይገባል።

ምስጢራዊነትን መጣስ ከInstacart መድረክ መታገድ ወይም ሥራ እንዲያቋርጡ መደረግ ወይም የአገልግሎት እድሎች መገደብ ሊያስከትል ይችላል።

## ማጭበርበር

በInstacart መድረክ ላይ የማጭበርበር ወይም የማታለል ድርጊቶች ሸማቾችን፣ ደንበኞችን፣ ቸርቻሪዎችን እና/ወይም Instacartን ሊጎዱ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት፣ የሚከተሉት ድርጊቶች፣ ያለገደብ፣ መታገድን ወይም ሥራ እንዲያቋርጡ መደረግን ወይም የአገልግሎት እድሎችን መገደብ ሊያስከትሉ ይችላሉ፦

- የክፍያ ካርድን አላግባብ መጠቀም፣ ገንዘብን ወይም ተመላሽ ገንዘብ የማግኘት ሙከራዎችን ማጭበርበር እንዲሁም ሕጋዊ Stripe የክፍያ ካርዶች የተጠቃሚ ውሎችን አለመከተል (እዚህ ተገልጿል)፤
- ሌሎች በማጭበርበር እንዲሳተፉ ወይም የመድረኩን አስተማማኝነት እንዲያበላሹ ማበረታታት፤
- ኩፖኖች፣ የደንበኝነት እና የአባልነት ፕሮግራሞች፣ የሪፈራል ጉርሻዎች ወይም ሌላ ማስተዋወቂያዎች ላይ ተፈጻሚ የሆኑ የInstacart የተጻፉ ውሎችን ወይም የቸርቻሮ ሻጮችን ደንቦች ወይም ፖሊሲዎችን አላግባብ መጠቀም።
- የጋራ-ሽመታ፡-
    - አገልግሎት ላይ ያለ እና የሚሠራ የInstacart ሸማች መለያ ለሌለው እና ተግባራቶቹ በInstacart መድረክ ለማይከናወኑ ሰው ኃላፊነቶችን መስጠት። በተጨማሪም ለደንበኛ ደኅንነት እና ግላዊነት ሲባል ትዕዛዙን የሚቀበል ሸማች ትዕዛዙን ወደ ደንበኛው በር ሲደርስ ሸማቹ መገኘት አለበት።
    - ለሌላ ሰው በማንኛውም ምክንያት የሸማችን መለያ እንዲከፍት መፍቀድ፣ ወይም በሌላ የሸማች መለያ አገልግሎት መስጠት፤
- የተደጋገሙ የሸማች መለያዎችን መያዝ፤
- በምዝገባ ወቅት ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተጭበረበረ መረጃ ለInstacart መስጠት ወይም በገለልተኛ የአገልግሎት ሰጪ ስምምነት ላይ ልክ ያልሆነ ወይም የተጭበረበረ ፊርማ ማቅረብ፣ የሐሰት ሪፖርት ማቅረብ ወይም የውሸት ሰነዶችን ማስገባት ወይም በሌላ መልኩ ሐቀኝነት በጎደለው መንገድ የInstacartን ንግድ ለማደናቀፍ መሞከርን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያተገደቡ፣ ተግባራ፤
- ትክክለኛ፣ የተሟላ እና ወቅታዊ የሸማች መለያ መረጃን መያዝ አለመቻል፤
- በሸማች ወይም በደንበኛ መለያ በኩል የሚካሄድ ማንኛውም የማጭበርበር ተግባር፣ አገልግሎት ለመስጠት ያጠፋውን ጊዜ ወይም የሸፈነውን ርቀት ማጭበርበርን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ያልተገደበ፤ እና
- የInstacart የንግድ ምልክት ወይም የአእምሮአዊ ንብረትን ሳይፈቀድለት መጠቀም።

### ጉልህ የሆነ የገለልተኛ አገልግሎት ሰጪ ስምምነት ጥሰት

የገለልተኛ አገልግሎት ሰጪ ስምምነትዎን ከጣሱ መለያዎ ሊታገድ ወይም ሥራ እንዲያቆም ሊደረግ ይችላል። ይህ በገለልተኛ አገልግሎት ሰጪ ስምምነትዎ ውስጥ ተብራርቷል። ጉልህ የሆነ የስምምነት ጥሰት የሙሉ አገልግሎት ሸማች መለያን መክፈቻ መመሪያዎችን የሚጥስ ማንኛውንም ድርጊት ያለምንም ገደብ ያካትታል።